# አማላጅነት

ከመንክር ብርሃኑ ትንሣኤ

የአማላጅነት ትምህርት በዘመነ አበው በሕገ ልቡና ፣ በዘመነ ኦሪት በመጻሕፍተ ብሉያት ፣ በዘመነ ሐዲስ በመጻሕፍተ ሐዲሳት የነበረና አሁንም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል ትምህርት እንጅ ከጊዜ በኋላ ድንገት የመጣ አይደለም ። ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችንም የቅዱሳት መጻሕፍትን የሐዋርያትንና የሊቃውንትን ትምህርትና ትውፊት መሠረት በማድረግ የአማላጅነትን ትምህርት ለምዕመናን በሰፊው ታስተምራለች። አማላጅነት እግዚአብሔር የሚፈቅደውና የሚወደው እንጅ ሰው ሠራሽ ልማዳዊ ወግ አይደለም ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ክርስትና ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የአማላጅነት ትምህርት ያለ እንጅ በኋላ ጊዜ ብቅ ያለ አይደለም ።

ዛሬ በሀገራችን ውስጥ በየአውቶቡስ ማቆሚያ፣ በመናፈሻዎች፣ በለቅሶ ቤት፣በሠርግ ቤት ፣ በመዝናኛ ሆቴሎች፣ቤት/ቤቶች፣ በመሥሪያቤቶች ፣ በመኖሪያ አካባቢዎች በገጠር በከተማ. . .እጅግ አከራካሪና አወዛጋቢ የሆነው ዐቢይ ጉዳይ በአማላጅነት ላይ የሚነሳው ጥያቄ ነው ። ሰዎች ስለአማላጅነት ያላቸው አቋም የሚከተሉትን እምነት የሚጠቁም በመሆኑ ያለዘ ውጣ ውረድ የሰዎችን የእምነት አቋም መለያ ሆኖአል ።

በዚህ ሳቢያ ወላጆችና ልጆች ባል ከሚስት ጓደኛ ከጓደኛ ጐረቤት ከጐረቤት ወዘተ ተቆራርጧል ። ተለያይቷል ። እኛ ኦርቶዶክሳውያን ጻድቃን ሰማዕታት ቅዱሳን መላእክት ይልቁንም እመቤታችን ቅ/ድንግል ማርያም ያማልዱናል ከፈጣሪያችን ዘንድ ያስታርቁናል ። ብለን የምናምነው እምነት የምንቀበለው ትምህርት የቅዱሳንን አማላጅነት ለማይቀበለው ሰው ጆሮውን የሚያሳክክ የእግዚአብሔርን ክብር የሚነካ ትምህርት መስሎ ይታያል ። በሌላ በኩል ደግሞ የቅዱሳንን አማላጅነት የሚቃወሙት ሰዎች ክብር ምስጋና ይግባውና የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጃችን ነው የሌሎቹን ፍጡራን ረዳትነት አንሻም የሚለው ትምህርት ለእኛ ለኦርቶዶክሳውያን ጆሮ የሚዘገንን የሚቀፍ ነው ።

እንደእውነቱ ከሆነ በሃይማኖት የምንመስላቸው ጥንታውያን የሆኑት የእስክንድርያ የሶሪያ ፣ የሕንድና የአርመንያ እኅት አብያተ ክርስቲያናት የቅዱሳንን አማላጅነት በሚገባ ይቀበላሉ በሃይማኖት ቀኖና( ዶግማ) ከኛ የሚለዩት ጥንታውያን የሆኑት የሮም ካቶሊክና የግሪክ የራሽያ የሮማንያ . . ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲሁ የአማላጅነትን ትምህርት ተቀብለዋል ። የቅዱሳንን አማላጅነት የሚቃወመው ትምህርት ብቅ ማለት የጀመረውና በኋላም የተስፋፋው ከ13ኛው — 16 ክፍለ ዘመን ውስጥ ይልቁንም በተሃድሶ (ሪፎርሜሽን) እንቅስቃሴ ጊዜ ነው ። የታሪክን ምስክርነት ካየን ይህ ትምህርት በቤክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ዘመናት እንደተነሱ የኑፋቄ አስተሳሰቦች በፍጻሜ ዘመን እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ የተመሰረተ እንግዳ ትምህርት ከጥንት ከመሠረት የመጣ አይደለም ። በየጊዜው የጥንቱን ትምህርት እየተው በእንግዳ ትምህርት መወሰድ እንዳይገባ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስጠነቅቃሉ ።

## ማማለድ ምን ማለት ነው ?

በግዕዝ ቋንቋ ተንበለ አማለደ ይላል "አማለደ" ማለት አንዱ ስለሌላው ለመነ ጸለየ ማለት ነው ማማለድ ማለት አንዱ ስለሌላው ችግር መቃለል መጸለይ መለመን ማለት ነው ። ይህ ትርጉም በማንኛውም ሰው ዘንድ የታወቀ የተረዳ ነው ። ምክኒያቱም በቀን ተቀን ሕይወታችን የምንፈጽመው ጉዳይ ስለሆነ ነው ። ስለአማላጅነት ስንናገር መታወቅ ያለባቸው ነገሮች አሉ ። ከትርጉሙ ስንነሳ በአማላጅነት ተግባር ውስጥ ሶስት ወገኖች መኖር አለባቸው እነሱም አማላጅ ፣ ተማላጅና የሚማለድለት ናቸው ሦስቱም ለአማላጅነት ሥምረት የተለያየ ድርሻ አላቸው ይህንንም በአጭሩ እንመለከታለን ።

ሀ. አማላጅ ፣ ማማለድ ለፍጡራን ባሕርይ የሚስማማ የትህትና ሥራ በመሆኑ አማላጆች ብዙ ናቸው በአጠቃላይ ሲነገር ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳን መላእክት ሲሆኑ እመቤታችን ደግሞ የአማላጆች ሁሉ የበላይ ነች።የአማላጆች ተግባር በኃጥአን ፈንታ ስለኃጥአን ወደ እግዚአብሔር ምልጃ ማቅረብ ነው ቅዱሳን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በጾም በስግደት ፣ በቁመት ወዘተ በጠቅላላ አስጨናቂ የሆኑ ጾዋትወ መከራዎችን እየተቀበሉ ልክ ለራሳቸው እንደሚለምኑ አድርገው ስለኃጥአን ይማልዱ ። እንዲያውም አንዳንድ ቅዱሳን የራሳቸውን ዘለዓለማዊ ደህንነት በኃጥአን መጽደቅ በመለወጥ ወደፈጣሪያቸው እንደሚለምኑ የሚከተሉት ሁለት ጥቅሶች ምስክር ናቸው ። "ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ወዮ እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ ።" ( ዘጸአ. ፴፪ ፡ ፴፩—፴፪) ይላል በሐዲስ ኪዳን ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ "ብዙ ኀዘን የማያቋርጥ ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ አልዋሽም ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል በሥጋ ዘመዶቼ ስለሆኑ ስለወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና በማለት ገልጿል (ሮሜ ፡ ፱፣ ፩—፫ በተጨማሪ ፩ዜና መዋ. ፳፩ ፡ ፲፯)

ለ= ተማላጅ ፡ ተማላጅ ማለት የአማላጁን ጸሎት ፣ ልመና ወይም ምልጃ ተቀባይ ወይም የምልጃ፣የልመና ፣ የጸሎት መድረሻ ማለት ነው ። በሃይማኖታችን ትምህርት ውስጥ የጸሎት ሁሉ መድረሻ እግዚአብሔር ነው ተማላጁ እግዚአብሔር እንደ አማላጆች ብዙ አይደለም አንድ ነው እንጅ ። አንድ እግዚአብሔር ስንል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ማለታችን ነው። ሦስቱ አካላት በአንድ ጌትነት ፣ በአንድ ሥልጣን ፣ በአንድ ክብር በአንድ መለኮት በአንድ ፈቃድ ወዘተ በሰማይና በምድር የሚገኙ የፍጡራንን ልመናና ምስጋና (ጸሎት) ተቀብለው የፈቃዳቸውንና ፣ የቸርነታቸውን ሥራ ይፈጽማሉ ። በሶስቱ አካላት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ መካከል የበላይና የበታች ጸሎት አቀባይ የለም ። "በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ ፡— በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ ። አራቱም እንስሶች አሜን አሉ ሊቃናቱም ወድቀው ሰገዱ " (ራእይ ፭ ፡ ፲፫ — ፲፬) በማለት ያረጋግጥልናል ።

ሐ= የሚማለድለት፡— አማላጆች ወደ እግዚአብሔር ምልጃ የሚያቀርቡት ስለኃጥአን ሰዎች መዳን ነው ። ርኩሳን መናፍስት ቢኖሩም የአማላጅነት በረከትና ቸርነት የተፈቀደውና የሚያገለግለው ለኃጥአን ሰዎች ብቻ ነው ። የሚጸለይለት ወይም የሚማለድለት ሰው ወይም ሕዝብ በአማላጅነት ሥራ ውስጥ የራሱ ድርሻ አለው ይኸውም በአማላጁ ጸሎት በተማላጁ ቸርነት ማመንና ከሚሠራው ኃጢአት የሚመለስ ። ተንሣሒ ልቦና ያለው መሆን አለበት አማላጆች አሉልኝ ብሎ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ቢሠራ አማላጆች ቅዱሳንን የኃጢአታችን ተባባሪ እግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሔርን ደግሞ የማይፈርድ ፈጣሪ ማድረግ ይሆናል ። እግዚአብሔር የአማላጆችን ምልጃ የማይቀበልበት ጊዜ አለ ይህም የሚሆነው የሚማልድለት ኃጥኡ በሠራው ኃጢአት የማይጸጸትና በዚያው የሚጸና ሲሆን ነው ለዚህም ቅዱስ መጽሐፍ "እግዚአብሔርም ሳሙኤልን በእስራኤል ላይ እንዳ ይነግሥ ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከመቼ ነው" (፩ሳሙ፣ ፲፮፥፩) እንዲሁም "እንግዲህ አልሰማህምና ስለዚህ ሕዝብ አትጸልይ ስለ እነርሱም ልመናና ጸሎት አታድርግ አትማልድላቸው እነርሱስ በይሁዳ ከተሞች ውስጥና በኢየሩሳሌም አደባባይ ላይ የሚያደርጉትን አታይምን ያስቆጡኝ ዘንድ ለሰማይ ንግሥት እንጐቻ እንዲያደርጉ ለሌሎችም አማልክት የመጠጥ ቁርባን እንዲያፈሱ ልጆች እንጨት ይሰበስባሉ አባቶችም እሳት ያነዳሉ ሴቶችም ዱቄት ይለውሳሉ እኔን ያስቆጣሉን ? ይላል እግዚአብሔር . ." (ኤር. ፯ ፣ ፲፮—፳) በተጨማሪ" እግዚአብሔርም እንደዚህ አለኝ ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደዚህ ሕዝብ አይዘነብልም ከፊቴ ጣላቸው ይውጡ ." (ኤር. ፲፭ ፥ ፩) በማለት ያስረዳል ።

## የአማላጆች አስፈላጊነት

የቅዱሳን አማላጅነት ያስፈለገበት ምክንያት ሀ/ጸሎታችን በፍጥነት ወደ እግዚአብሔር ስለሚደርስልንና ለ/ፈጣሪያችን የወዳጆቹን ይልቁንም የእናቱን የድንግል ማርያምን ጸሎት ተቀብሎ ስለ ቅዱሳን ይልቁንም ስለ እናቱ ብሎ የቸርነቱን ሥራ ስለሚሠራልን ችግራችንን ስለሚያቃልልን ነው ። የቅዱሳንን ጸሎት ከኃጥአን ጸሎት ይልቅ እንደ ሚሰማ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ።

" የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው (ልመናቸው) ናቸው . . ." (መዝ. ፴፫ ፣ ፲፭—፳፪)

"የኃጥእ ሰው ፍርሃት በላዩ ይመጣበታል የጻድቃንም ምኞታቸው ትሰጣቸዋለች" (ምሳ. ፲ ፣ ፳፬)

"የኃጢአን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው የቅኖች ጸሎት ግን በእርሱ ዘንድ የተወደደ ነው" (ምሳ. ፲፭ ፣ ፰

" እግዚአብሔር ከኃጥአን ያርቃል የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል" (ምሳ. ፲፭ ፣ ፳፱)

"በእኔ በትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል ።" (ዮሐ. ፲፭ ፥ ፯)

" የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕ. ፭ ፣ ፲፮—፲፰)

"ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው የዕጣኑም ጢስከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ" (ራእይ ፰፥፫—፬) ወዘተ.

የቅዱሳን ጸሎት በፈጣሪ ዘንድ ተወዳጅ ሊሆን የቻለው ቅዱሳን ሰውነታቸውን ከቂም ከበቀል ከኃጢአት ስላነጹ እግዚአብሔር የማይወደውን ልመና ስለማይለምኑና ልመናቸው እንደሚፈጸም በፍጹም ልብ እምነው ስለሚጸልዩ ነው ይህንንም በሚከተሉት ጥቅሶች እንመለከታለን ።

" የጻድቃን ምኞት በጎ ብቻ ነው የኃጥአን ተስፋ ግን መቅሰፍት ነው "

" የጻድቃን ሐሳብ ቅን ነው የኃጥአን ምክር ግን ተንኮል ነው "

" በዚያን ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር እየሰገደችና አንድ ነገር እየለመነች ወደ እርሱ ቀረበች እርሱም ምን ትፈልጊያለሽ አላት እርስዋም እነዚህ ሁለቱ ልጆች አንዱ በቀኝህ አንዱ በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለቸው ጌታችን ኢየሱስም የምትለምኑትን አታውቁም አላት "

" . . ስለዚህ እላችኋለሁ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል" (ምሳ. ፲፩ ፥ ፳፫ ምሳ. ፲፪ ፥ ፭ ማቴ. ፳ ፥ ፳—፳፪ ማር. ፲፩ ፥ ፳፬

ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳን መላእክት ኃጥአን ምህረትን ሲያገኙ እጅግ ደስ ይላቸዋል ። እግዚአብሔርም የሚወዳት ቅድስት እናቱና የሚወዳቸው ቅዱሳን ወዳጆቹ ስለኃጥአን ምህረት ሲለምኑት እናቱና ወዳጆቹን ለማስደሰት ሲል ልመናቸውን ሰምቶ ይፈጽምላቸዋል ። ይህንንም ጌታችን በወንጌል "እላችኋለሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኙ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል" "እላችኋለሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል" (ሉቃ. ፲፭ ፥ ፯ ፣ ፲)

" በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል እስከአሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ "(ዮሐ. ፲፮ ፥ ፳፫—፳፬) በማለት ገልጿል ።

አማላጅነት የእግዚአብሔርን ክብርየሚጋፋ ሳይሆን የበለጠ ፈጣሪን የማክበር ምልክት ነው። ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር ራሱ ሰውን ወደአማላጅ የመራበት ጊዜም አለ። አምላካችን እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ መቅሰፍት ከመምጣቱ በፊት ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ያሳውቃል ። ለምሳሌ ዓለምን የደመሰሰውን የጥፋት ውሃ መምጣት ለኖኅ ፣ የሰዶም የገሞራን ጥፋት ለአብርሃም ፣ የነነዌን ሰዎች ኃጢአት ለዮናስ የእስራኤሎችን መማረክ ለነቢያት ገልጿል።

እግዚአብሔር ለወድጆቹ አስቀድሞ የሚገልጽበት ምክንያት፡— ሀ/ ሕዝቡን አስተምረው መክረው ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር በንስሐ እንዲመልሱትና ለ/ስለ ሕዝቡ ኃጢአት እግዚአብሔርን መዓቱን በምህረት ቁጣውን በትእግሥት እንዲመልስ በጸሎት እንዲያማልዱ ነው።

## በአፀደ ሥጋ ያሉ ቅዱሳን እንደሚ... ማልዱ

በአፀደሥጋ (በሕይወተ ሥጋ) ያ... ቅዱሳን እንደሚያማልዱ በርካታ መ... ሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አሉ ። እንደ... ውነቱ ከሆነ ማንኛውም ክርስቲያን ለ... ላው ወንድሙ እንዲፀልይ ታዟል ። ባ... ቤቱ መድኃኒዓለም ያስተማረን " አቡ... ዘበሰማያት " ጸሎት ለራሳችን ብቻ ሳ... ሆን ለሌላውም ጭምር የምንፀልየ... ጸሎት ነው ። ምልጃ በክርስቲያኖች የ... ሎት ተግባር ውስጥ ሰፊ ስፍራ አለ... ለዚህ ቅ ጳውሎስ " እንግዲህ እግዚአ... ሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁ... ጾጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመና... ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለሰዎች ሁ... ስለነገሥታት ስለመኳንንትም ሁሉ እን... ደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ... ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ... ወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔ... በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚ... ያሰኝ ይህ ነው ( ፩ ጢሞ ፪ ፥ ፩—፬ ) ጌታ... ቅርብ ነው በነገር ሁሉ በጸሎትና በ... ልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንደ... ልመናችሁን አስታውቁ እንጅ በአንዳች... አትጨነቁ " ብሏል ( ፊልጵ ፬ ፥ ፮) ነቢ... አሳይያስም " እግዚአብሔርም አየ ፍ... ድም ስለሌለ ተከፋ ሰውም እንደሌ... አየ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌ... ተረዳ ተደነቀም . . "(ኢሳ. ፶፱፥፲፮) ብሏል... ጌታችን በወንጌል " በሰማያት ላለ አባ... ታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻች... ሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁን መርቁ... ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ... ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ" (ማቴ. ... ፵፫፥—፵፮ ) በማለት እንኳን ለወዳጆቻችን... ለጠላቶቻችንም ቢሆን መጸለይ እንደሚገባ... አዞናል አማላጅነት በሁሉ የታዘዘ ቢሆንም በዚህጽሁፍ ውስጥ የምንመለከተው የፍ... ጹማንን አማላጅነት ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ጋር በማገናዘብ በጥሞና እንመልከት ።

በባህርም ማዕበል መካከል በየብስም መካከል ተመላለስሁ ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን አስቀድሞ የሕዝቡንና የአህዛቡን ሥጋ አልተዋሃድኩም

መጽሐፈ ሲራክ ፳፬-፯

፩ በዘፍጥ ፲፰ ፥ ፲፯—፴፫ ውስጥ ሥላሴ በአብርሃም ቤት በእንግድነት ከተገኙ በኋላ ወደሰዶምና ገሞራ ሲሄዱ "እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን በማለት ስለሶዶም ኃጢአት በነገሩት ጊዜ አብርሃም እንዴት እንዳማለደ ይገልጻል የአብርሃም ምልጃ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ቢኖረውም በከተማይቱ ፲ ጻድቃን ስላልተገኙ አንድ ሎጥ ብቻ በመገኘቱ ከተማይቱ ወደመች ።

፪/ በዘፍጥ. ፲፱ ፥ ፲፰—፳፪ "የተናገርሃትን ከተማ እንዳላጠፋት እነሆ በዚህ

ነገር የለመነከኝን ተቀብዬልሀለሁ . . .'' በማለት እንደሰዶምና ገሞራ ልትጠፋ የነበረች ከተማ ሎጥ ሸሽቶ ስላረፈባት መላእክት ስለሎጥ ልመና ሳያጠፏት ትተዋታል ።

፫/ በዘፍጥ. ፳ ፡ ፩— ፲፰ የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ የአብርሃምን ሚስት ሣራን ለሚስትነት ስለወሰዳት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ቤተሰቡን በሙሉ እንደሚቀስፍ እንዲህ አለው'' እኔ ደግሞ በፊቴ ኃጢአት እንዳትሠራ ከለከልሁህ ስለዚህም ትነካት ዘንድ አልተውኩህም አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና ስለአንተ ይጸልያል ትድናለህም ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ'' አለው ንጉሡም እንደታዘዘው አደረገ ''አብርሃምም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ እግዚአብሔርም አቢሜሌክን ሚስቱንም ባሪያዎቹንም ፈውሳቸው በአብርሃም ሚስት በሣራ ምክንያት በአቢሜሊክ ቤት ማኅፀኖችን ሁሉ በፍጹም ዘግቶ ነበርና'' በማለት ተገልጿል ።

፬/ ዘጸአ. ፴፪ ፡ ፯—፲፬ ላይ እስራኤሎች የወርቅ ጥጃ ባመለኩ ጊዜ ''እግዚአብሔር ሙሴን እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ ። አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሁለሁ'' ብሎታል ። እግዚአብሔር ሙሴን ሳያማክር ማጥፋት ይችል ነበር ''እንዳጠፋቸውም ተወኝ'' የሚለው አነጋገር አትማልድላቸው እንደማለት ነው ሙሴ ግን ወደፈጣሪው ስላማለደ ''እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፉት ራራ'' ይላል ። ይህን የሙሴን አማላጅነት ቅ/ ዳዊት በመዝሙሩ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ብሎታል ። ''በኮሬብ ጥጃን ሠሩ ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ ሣር በሚበላ በበሬ ምሳሌ ክብራቸውን ለወጡ ታላቅ ነገርንም በግብጽ ድንቅንም በካም ምድር ግሩም ነገርንም በኤርትራ ባሕር ያደረገውን ያዳናቸውንም እግዚአብሔርን ረሱ እንዳያጠፋቸውም ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ'' ብሏል (መዝ.፻፭ ፡ ፲፱—፳፫

፭/ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ ምክንያት አሮንና ማርያም በወንድማቸው በሙሴ ላይ ስላንጎራጎሩበት እግዚአብሔር ለሙሴ ተቆርቁሮ ከገሠጻቸው በኋላ እህቱ ማርያም ለምጻም ሆነች በዚህ ጊዜ አሮን ደንግጦና ተጸጽቶ ''ጌታዬ ሆይ ስንፍና አድርገናልና በድለንማልና እባክህ ኃጢአት አታድርግብን'' በማለት ወንድሙን ሙሴን ለመነው ሙሴም ወደፈጣሪው አማልዶ ከለምጿ ተፈውሳለች ። ዘኁል. ፲፪ ፡ ፩—፲፮) ።

፮/ እስራኤላውያን ስለዔናቅ ልጆች በሰሙ ጊዜ ወደ ግብጽ ለመመለስ አስቡ በሙሴና በአሮንም ላይ አንጐራጐሩ እግዚአብሔርም ሙሴን '' ይህ ሕዝብ እስከመቼ ይንቀኛል በፊቱ ባደረግሁት ሁሉ እስከመቼስ አያምኑብኝም ከርስታቸው አጠፋቸው ዘንድ በቸነፈር እመታችዋለሁ . . . '' ሲለው ሙሴ እንደ ወትሮው ወደ አምላኩ ጸለየ ''ይህን ሕዝብ ከግብጽ ምድር ካወጣህ ጀምሮ ይቅር እንዳልሀቸው እባክህ እንደምህረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል ።'' አለው ። ''እግዚአብሔርም እንደቃልህ ይቅር አልሁ'' አለው ይላል (ዘኁል. ፲፬ ፡ ፩—፳)

፯/ ዳታንና አቤሮን በምቀኝነታቸው ከነቤተሰቦቻቸው ምድር ስለዋጠቻቸው ፣ ሁለት መቶ ሃምሳ ሰዎች ደግሞ በትዕቢታቸው እሳት ከሰማይ ወርዶ ስለበላቸው ''የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እናንተ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ገድላችኋል ብለው በሙሴና በአሮን ላይ አንጐራጐሩ'' እግዚአብሔርም ተገልጾ ሙሴን '' ከዚህ ማኅበር መካከል ፈቀቅ በሉ እኔም በቅጽበት አጠፋችዋለሁ አለው '' ሙሴና አሮንም በግምባራቸው ወድቀው ጸለዩ ሙሴም አሮንን '' ጥናህን ውሰድ ከመሠዊያውም ላይ እሳት አድርግበት እጣንም ጨምርበት ወደማኅበሩ ፈጥነህ ውሰደው አስተስርይላቸው ከእግዚአብሔር ፊት ቁጣ ወጥቶአልና መቅሠፍትም ጀምሮአል'' አለው ። አሮንም ሙሴ እንዳለው አደረገ መቅሰፍቱም ተከለከለ (ዘኁል. ፲፮ ፡ ፵፩ —፶)

፰/ እግዚአብሔር ኤልፋዝ ፣ በልዳዶስና ሶፋር የተባሉትን የኢዮብን ጓደኞች ''እንደባሪያዬ እንደኢዮብ ቅንን ነገር ስለእኔ አልተናገራችሁምና ቁጣዬ ነድዶአል አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ የሚቃጠልንም መሥዋእት ለራሳችሁ አሳርጉ ባሪያዬም ኢዮብ ስለእናንተ ይጸልያል እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ እንደባሪያዬ ቅን ነገር አልተናገራችሁምና ።'' ስላላቸው በአምላክ እንደታዘዙ አደረጉ ። ኢዮብም ስለጓደኞቹ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ። ''እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት (ጸሎት) ተቀበለ ።'' ይላል (ኢዮ. ፵፪፡ ፯—፱)

፱/ በትንቢተ ኤርምያስ ፵፪ ፡ ፩—፲፪ እንደተገለጸው ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሕዝቡ ሁሉ ወደኤርምያስ ቀርበው ''እባክህ በፊትህ ልመናችን ትድረስ አምላክህም እግዚአብሔር የምንሄድበትን መንገድና የምናደርገውን ነገር ያሳየን ዘንድ ስለእኛ ስለዚህ ቅሬታ ወደ አምላክህ ወደእግዚአብሔር ጸልይ አሉት'' ኤርምያስም እነሆ እንደቃላችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ የማመልስላችሁን ሁሉ እነግራችኋለሁ ከእናንተ ምንም አልሸሽግም አላቸው'' ።

፲/ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ አንዲት ከነናዊት ሴት ''ጌታዬ የዳዊት ልጅ ማረኝ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል'' ብላ ብትጮህ ጌታችን ምንም ሳይመልስላት ዝም ባለ ጊዜ ሐዋርያት ቀርበው እንደ ባለሟልነታቸው ''በኋላችን ትጮኻለችና አሰናብታት እያሉ ለመኑት'' ጌታም የሐዋርያትን ልመና ሰምቶ የሴትዮዋን እምነት አይቶ የለመነችውን ልጅዋን ፈወሰላት (ማቴ. ፲፭ ፡ ፳፩-፳፰) ። . . .

፲፪/ ቅዱስ እስጢፋኖስ አይሁድ በሚወግሩት ወቅት ተንበርክኮ ''ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው'' በማለት እንደለመነላቸው ተጽፎአል (የሐ. ሥራ ፯ ፡ ፷) ፲፪/ቅ/ያዕቆብም ።

''ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ሰው ስለሌላው ይጸልይ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች ።'' (ያዕ. ፭ ፡ ፲፮—፳) በማለት ሐዋርያዊ መመሪያ ሰጥቷል በተጨማሪ ፪ ቆሮ. ፭፡፲፰-፳፩ ፩ ዮሐ.፭፡፲፮ ይመልከቱ በዚህ መሠረት ቅዱሳን ሰዎች ስለኃጥአን የሚለምኑት ልመና ተቀባይነት ስላለው በአማላጅነት መጠቀም ታላቅ ብልህነት ነው ።

ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ እንደሚያማልዱ ለማሳየት ተሞክሮአል ። በሚቀጥለው ጊዜ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሆነው ማማለድ እንደሚችሉ እናቀርባለን ። ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን ●